EthioLion

ዴሞክራሲያ

# ያልታበሰ እንባ፤ ያልተቀረፈ ችግር፤ የቀጠለ ትግል

## (ኢሕአፓ የታወጀበትን ነሐሴ 26/1967 ን ማስታወሻ )

**ልዩ ዕትም** **ነሐሴ 26/2002**

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ዓመት አልፎ ዓመት ሲተካ፤ አንዱ አገዛዝ በሌላው ሲቀየር፤ የትላንት ደይን በብሩህ ጎሕና ፀሐይ ይተናል ብሎ ተስፋውን በፀሎት ሳይቀር እያጀበ ቢጠብቅም ፍላጎቱ አልሟላ እያለ ፤እንባውን አባሽና ችግሩን አስወጋጅ እያጣ፤ ስቃዩ በመቀጠሉ ፤ ያ መራራ ሕዝባዊ ትግል የግድ ቀጣይ ሆኖ፤ ሀገርም እንደገና መስዋዕትነትን ጠያቂ ሆና በመገኘቷ፤ መራራው ትግል ከመቀጠል ሌላ አማራጭ አጥቶ እነሆ ያልታበሰ እንባ፥ ያልተቀረፈ ችግር ቀጣይ ትግልን ግዳጅ አድርጎብን ይገኛል:: ሀገር ማዳን የሚቻለው በትግል ብቻ ስለሆነ መታገል የግድ ሆኗል::

የኢትዮጵያ ዋና ዋና ችግሮች ሁሉ በነበሩት አገዛዞችና የተፈጠሩና ባለው ዘረኛ ቡድን የቀጠሉ መሆናቸው የማይካድ ሐቅ ነው:: እነዚህ መሠረታዊ ችግሮችም ሊፈቱ ባለመቻላቸው--አገዛዞቹ መፍትኄ አመንጭዎችን በማፈናቸው-- ለለውጥና ለእድገት የሚደረገው ትግል የማያባራ ሆኖ ሀገሪቷ በጦርነትና በመከራ መሰቃየቷ ቀጥሏል:: በአፄው ዘመን የኢትዮጵያ ብዙኀን አርሶ አደሮች በመሆናቸው በገባርነትና ጪሰኝነት ተቀፍድደው ምርታቸውን ለባላባቶችና በዝባዦች እየገበሩ ሲሰቃዩና መብት አልባ ሆነውም ሲረገጡ ነበርና መሬት ለአራሹና ዴሞክራሲያዊ መብት ለሕዝብ የሚሉት ጥያቄዎች የሕዝቡ ጥያቄዎች ሆኑ፤ዛሬም ናቸው:: የሕዝብ እኩልነት መረጋጋጡና በሃይማኖት በኩልም ተከስቶ የነበረው ልዩነት መወገዱና ባጠቃላይም ጭቆና አክትሞ ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መመሥረቱ ዋና ተግባር ነው መባሉም አለምክንያት አልነበረም ማለት ይቻላል:: ለጥገና ለውጥ ጆሮ የማይሰጥ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ስለነበርም ለውጥ ፈላጊውና የነቃው ክፍል

Ethiolion.com

EthioLion



ዘመናዊና ታጋይ ፖለቲካ ድርጅትን መመሥረት ግዳጅ ሆኖበት በዚሁም መሠረት ለለውጥ ለመታገል በሚል ኢሕአፓ በሚያዝያ 1964 ዓ.ም. ሊመሠረት በቃ።

ለሁሉም ጊዜ አለው እንደሚባለው የድርጅት መከሰትም ሆነ የቅራኔዎች ይዘት አብዮታዊ መፍትሄን መሻት በዘፈቀደ የሚመጡ ሳይሆን የተጨባጩ ሁኔታ ውጤቶች ናቸው። የጭቆናና የብዝበዛ ሥርዓት በሕዝባዊ አመፅ መፈተሹ ወይም መወገዱ የማይቀር ነው። ገዢዎች በለመዱት መንገድ መቀጠላቸውና ተገዢው ሕዝብ ደግሞ በተለመደው መንግድ ሊገዛና ሊኖር ባለመፈለጉ ቅራኔው ፈንድቶ አብዮት ሊመጣ መቻሉ የተፈጥሮ ሕግ ነው ሊባል ይችላል። የየካቲት 66 አብዮት ፍንዳታ ግብታዊ ነበር ቢባልም ለዓመታት የተካሄዱት ትግሎች--የአርሶ አደሩ አመጾች፥ የሠራተኛው የመደራጀትና የሥራ ማቆም ትግሎች፥ የተማሪዎች ሰልፎች፥ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራዎች ወዘተ ---ለየካቲት 66 መፈንዳት ድልዳል ያነጠፉ ናቸው። ሥርዓቱ ሊያቆመው የሚችለው ክስተት አልነበረም። ለለውጥ ሲታገሉ የነበሩትም ቢሆኑ ፍንዳታውን ቀድመው ያወቁት አልነበሩምና ዝግጅታቸውም የተዳከመ ነበር። ይህም ሁኔታ የኋላ ኋላ የሕዝብን ድል ሊያስከብር በሚችል ደረጃ የተዘጋጀ ኃይል ባለመኖሩ ድሉን የታጠቁ መኮንኖች እንዲቀሙ ረድቷቸዋል። የቅርብ ታሪካችንን ስንቃኝ ይህ ድክመት የሕዝብን ትግል እያጀበና እየጎዳ ሁሌም የሕዝብትግል በአምባገነኖች እየተቀማ ወይም እየተጨናገፈ የጭቆናው ሥርዓት ቀጥሏል። በ1983 ሆነ በ1997 የተከሰተው ይኸው ነው። ሕዝብ የትግሉን ውጤትና ድሉም ሊያስከብር ይችል ዘንድ ድርጅትና ትጥቅ--ጉልበት--ያስፈልገዋል። ይህ ካልተሰናዳ ኃግሮ ለሌላ በዪ ማቅረብ ይሆናል ትግሉ ሁሉ--ባለጉልበት ድሉን ከሕዝብ ይቀማዋልና።

ኢትዮጵያ ነፃነቷን ጠብቃ የቆየችውና ለሚሊዮኖችም አርአያ ሆና የተገኘችው በልጆቿ መስዋዕትነት መሆኑ ይታወቃል። ነፃነቷን ለመድፈር አያሌ ባዕዳን ሞክረው ነበር። ዛሬ ወያኔ ሀገሪቷን ከፍቶ የሰጣቸው ቱርኮች፤ ግብፆችና ሱዳኖችም ቢሆኑ ቀደም ሊወሯት የሞከሩ ነበሩ። ጣሊያንና እንግሊዝም ቢሆኑ ብዙ ሙከራዎችን አድርገው በተለይ ከሚሊዮን በላይ ዜጎቻችንን ፈጅቷል። ባዕዳን ኢትዮጵያን ሉዓላዊነቷን ለማሳጣት ሲጥሩ ባጅተዋል። ይህ የታሪካችን ቀጣይ ገፅታ ሆኖ የቆየ ነው። ይህ ቢባልም የኢትዮጵያ መሠረታዊና ቀጣይ ችግሮች ግን ውስጣዊ አምባገኖችና አገዛዞቻቸው ለመሆናቸው ጥርጥር የለውም። ለባዕዳን ጥቅም ተገዢ የሆኑ ሀገረ በቀል መዥገሮችበመኖራቸው ባዕዳን በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ላይ አደጋ መጣል መቻላቸው ዛሬም ቀጥሎ ያለ መወገድ ያለበት ሁኔታ ነው። ግን በአፄው ዘመን ጀምሮ እስካሁን ተቃውሞና ትግልን “ በውጭ እጅ የተቀሰቀሰ ” በሚል ለማጥላላት የሚደረገው ጥረት መሠረተ ቢስና በሀሰት ላይ የተመሰረተ መሆኑ ግልፅ ነው። የባዕድ ርዕዮት አራማጆች፤ በአረቦች የተገዙ፤ በመስኮብ የተደራጁ ወዘተ...ሲባል የነበረወና ዛሬም

EthioLion



በሌላ መልክ ግን በዚያው ቅኝት የቀጠለው ሊሸፋፈን ያልቻለው ሐቅ ግን የኢትዮጵያ ችግሮች በመጀመሪያ ደረጃ የራሷ የኢትዮጵያ መሆናቸውንና ከዴሞክራሲና ሕዝባዊ ሥርዓት መጥፋት ጋር የተያያዘ መሆኑን ነው፡፡ ኢሕአፓም ሊመሠረት የቻለው ማንም ባዕድ ወይም የውጭ ኃይል አነሳስቶት ሳይሆን የሀገሪቷ ተጨባጭ ሁኔታና የቅራኔዎች ደረጃ የኢሕአፓ ዓይነት ድርጅትን የሚወልድበት ጊዜ በመድረሱ ነው፡፡ የሀገሪቷ መሠረታዊ ችግሮች--የዴሞክራሲና እኩልነት አለመኖር፤ መብት በመታፈኑ፤ ብዙዎች በጥቂቶች መበዝበዛቸው-- ውስጣዊ ናቸው፡፡ በነዚህ ሁኔታዎች በተለይም ሥልጣንና ንዋይ አፍቃሪ ገዢዎች በሕዝብ ላይ አለፍቃዱ በመጫናቸው ባዕዳን በመጠቀም አምባገነኖቹን እየገዙና በቅጥረኛነት እያሰለፉ ኢትዮጵያን ሲጎዱ ቆይተዋል፡፡ አፄው ለአሜሪካ፤ አረመኔው መንግሥቱ ለሶቭየት ኅብረት፤ ወያኔ እንደገና ለአሜሪካናለምዕራቡ ሀገርን ሸጠው ወይም አንበርክከው ለሎሌነታቸው ደግሞ የባዕዳንን ድጋፍ አግኝተው ሥልጣናቸውን ሊያራዝሙ ችለዋል፡፡ በመሆኑም ለችግሮቹ መፍትኄ ፍለጋ በቅድሚያ ውስጣዊ ቅራኔው ላይ በማተኮር ሀገራዊ ምላሾችን ለመስጠት መጣር ይገባዋል ማለት ነው፡፡ ባለቤቱ ያቀለለውን አሞሌ ባለዕዳ አይቀበለውም እንደተባለው ኢትዮጵያ በገዛ ገዢዎቿ ተጋልጣ ስትገኝ ለዚህጥፋት ዋናው ተጠያቂ ባዕዳን ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ሀገራችንን የሚጎዳ  ድርጊታቸውንና ሴራቸውን ሁሉ መቃወማችን ተገቢ ቢሆንም ሀገርን ለማስከበር ግን በቅድሚያ በከሀዲው አገዛዝ ላይ መነሳት አለብን ማለት ነው፡፡ ይህን ሐቅ ከተረዳን ወይም መረዳት ሲገባን ዓመታት አልፈዋልና ዛሬም ኢትዮጵያ የገባችበትን አሳዛኝ ሁኔታ ለመለወጥ የባዕዳንን ሚና ማቀጨጭ ግዴታችን ሆኖእያለ ዋናው ምታችን  መደቆስ ያለበት ግን  የወያኔን ቡድን ነው፡፡

መሠረታዊ ችግሮች ሊቀረፉ ብቻ ሳይሆን ሊወገዱ የሚችሉት ችግሮቹ መኖራቸው በመጀመሪያደረጃ ከታወቀና ከታመነ ነው፡፡ በሽታውን የደበቀ መድኃኒት አይገኝለትም እንደሚባለው የአፄው አገዛዝ ፈላጭ ቆራጭ፤ የደርግ ሥርዓት ፍፁም አምባገነናዊ፤ የወያኔ አገዛዝ ደግሞ ዘረኛና ፀረኢትዮጵያ መሆናቸውን መካድ ሳይሆን ማወቅና ሁሉ ሥርዓቶች ሕዝብን መበደላቸውንና መብትአልባ ማድረጋቸውን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ሁሉም ሥርዓቶች የጥቂቶች እንጂ የብዙኀኖች አልነበሩም፤ አይደሉምም፡፡ የሕዝብ እኩልነት በሶስቱም አገዛዞች እውን አልሆነም፡፡ የዴሞክራሲ ጭላንጭል በፊትም አልታየም፤ ዛሬም የለም፡፡ ያለፉት ሁለቱ አገዛዞች ፀረ ዴሞክራሲ በመሆናቸውና ሕዝብን በመበደላቸው ሀገርን ጎዱ ቢባሉም እንደ አሁኑ ወያኔ ኢትዮጵያን እንደ ሀገር ለማጥፋትና ለማዋረድ የተነሱ አልነበሩም፡፡ ኢሕአፓ ከተመሠረተ ጊዜ ጀምሮ ያለውን ችግር ሁሉ አፍረጥርጦ በማውጣት ይሆናሉ ይበጃሉ ያላቸውን መፍትኄ ለመጠቆምና በሥራ ለማዋል ጣረ እንጂ ችግሮቹ የሉም ብሎ የሰጎን ፖለቲካን አልመረጠም፡፡ በነበረው ተመክሮ ማነስ ምክንያት ድርጅቱስህተቶችን መፈፀሙ አይቀሬ ቢሆንም በመሠረቱ የሕዝብን መፈክሮች አንግቦ

EthioLion



በመታገል ለትግሉ ትልቅ አስተዋፅዖን አድርጓል፡፡ ያሉትን ችግሮች በሚገባ ማወቅና ለነዚህም መፍትኄ ለመሻት መነሳት ያስፈልጋል እንጂ ችግሮቹ አልነበሩም/የሉም ብሎ መደምደሙ የሀገርን ችግር አያስወግድም፡፡ ለዚህም ነው ዛሬም ቢሆን ያለው አገዛዝ ማን እንደሆነና ለማን እንደቆመ በሚገባ በመረዳት፤ የሕዝብ ችግሮች ምንድ ናቸው የሚለውን ጠንቅቆ በማወቅና በውዝንብር ባለመነከር ለወጥን በትግል ለማምጣት ቆርጦ መነሳት የግድ ይሆናል፡፡

ሕዝብ አሁንም የምፀት ዕንባውን እያፈሰሰ ነው፡፡ ችግሮቹ አልተቀረፉም፡፡ የመሬቱና የሀገሩ ባለቤት አልሆነም፤ መብት አልባነቱም ቀጥሏል፡፡ ይባስ ብሎ የሀገር ህልውና ሲሸረሸር ማየት ተገደናል፡፡ ለወጥ የለም--የለውጥ ወሬ ግን ደርቷል፡፡ ኢትዮጵያ ዛሬም ለብዙኀኑ የስቃይና የእንባ፤ የረሀብና የሰቆቃ ሀገር ናት፡፡ ለጥቂቶች የአድዋ ምርጦችና ጀሌዎቻቸው ግን መፈንደቂያና መጫወቻ ሆና ትገኛለች፡፡ ባለፉት 19 ዓመታት ወያኔ በሀገር ሲጫወትና ዜጎችን ሲገደል ሲበድል በየጊዜው የተካሄዱ ትግሎች ትምህርታዊነታቸውም የሚካድ አይደለም፡፡ ይህን ትምህርት መቅሰም ደግሞ ለኢትዮጵያ ህልውና መጠበቅ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ስንት ትውልድ፤ ስንት መቶ ሺ ጀግናና አርበኛ ሕይወቱን ገብሮ አስከብሮ ያቆያትን ሀገር ወያኔ ለባዕዳን አሳልፎ ሰጥቷታል፡፡ ህንድ በጋምቤላ ፤ ሱዳን በቋራ፤ ግብፅ በባህርዳር፤ አረቦች በደቡብ፤ ቻይና በየቦታው በሕዝብ መሬትና መብት ላይ የባለይነትን በወያኔ ተለግሰዋል፡፡ ደበቅ ያለ እጅ አዙር ቅኝ አገዛዝነት በኢትዮጵያ ላይ በመጫን ላይ ነው፤ ሀገሪቷ ለቅርጫ ቀርባለች፡፡ ቅድመ የካቲት ተነስቶ የነበረው የሉዓላዊነት ጥያቄ ዛሬም-- ያውም በይበልጥ-- አንገብጋቢ ነው፡፡ ከዚህ አልፎ የራሱ የወያኔ አገዛዝ የደረሰበትየዘረኝነት ደረጃ ወያኔ ራሱን ቅኝ ገዢ እያስመሰለው ነው የሚለው ክስ በቀላሉ የሚተን አይደለም የሚሉም ብዙ ናቸው፡፡ ኢሕአፓ ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ሊታገል ከተነሳ 38 ዓመት የተቆጠረሲሆን ዛሬ ደግሞ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ፀረ ወያኔው ትግል ሉዓላዊነትን ማስከበር በሚል ከባድግዳጅንም ያቀፈ መሆኑን ይገነዘባል፡፡ የዴሞክራሲው ትግል ዛሬ አንገብጋቢ በሆነው ሀገር ማዳን ትግል ታጅቦ ተነሱ ታገሉ እያለ ነው፡፡ ለዚህም ነው የፀኑና የማያወላውሉ ፀረ ወያኔ ደርጅቶች የሚያስፈልጉት፡፡

የትግል ስልትን ሆነ ይዘት ወሳኝ ገዢው ክፍል ሊሆን አይችልም፡፡ የወያኔ አገዛዝን እንዴትና በምን ዓይነት መታገል እንደሚገባ ወሳኙ ተጨባጩ ሁኔታ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃም ኃያል ነው በሚል ፈቃድ የሚጠየቅ ሀገር ወይም ኃይል የለም፡፡ ሕዝብ ያስፈልጋል፤ ያዋጣልና ይገባል ባለው መንገድ መታገል መብቱ ብቻ ሳይሆን ግዴታው ነው፡፡ ሕዝብ ፀረ ኢትዮጵያውን የወያኔ አገዛዝ በሁለገብ ትግል በጊዜ እንዳይጋፈጥ በሰላማዊ ትግል ሽፋን እጅ መስጠትን የሰበኩት ወያኔዎች ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች ራሳቸውንም የሕዝብ ሊሉ የከጀሉ

EthioLion



**ድርጅቶችም መሆናቸውን ሕዝብ ያውቃል፡፡ ጠላትን በተመለከተም ግንዛቤም በመንሸዋረሩ ጠላትነቱን በተመለከተ ሊጨበጥ ይገባ የነበረው ቁርጥ አቋም  የሁሉም ሊሆን አልቻለም፡፡ ተለጣፊና ሆዳሙ ብቻ ሳይሆን ተቃዋሚ በሉኝ ያለውም ቢሆን ከአረመኔው ገዢ ቡድን ጋር መቆራረጥን ሊመርጥ አልቻለም፡፡ እንዲያውም ቢከፍቱት ተልባ ሆኖ አንዳንዱ ተቃዋሚ ተፎካካሪም ለመባል ብቃቱ ያነሰውና ተቃወምኩት ካለው ቡድን ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በ** 1997 **ምርጫ ሂደትና ሁኔታ እንደታየው የሕዝብ ትግል በተደጋጋሚ ምት የደረሰበትና ግቡን ማግኘት ያቃተው መሪዎችህ ነን ባሉት ድክመት መሆኑን መካድ አይቻልም፡፡ የተቃዋሚ ኃይሎችን ህብረት ያኮላሸውና አልፎም እንዲያብሩ ጋሬጣ የሆነው ወያኔ ብቻውን አይደለም፡፡ አዜው በጊዜያቸው ሥዩመ መለኮት የተባሉ ሲሆን ነፍሰ ገዳዩ ኮሎኔልም ቆራጡ መሪያችን ሲባል እንደነበር የሚረሳ አይደለም፡፡ በተወሰነ ደረጃ ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን መደናገር በመስፈኑና ጠላት ጠላት ተብሎ ባለመወሰዱ የሕዝበን ትግል መጓተቱና መጎዳቱም የታየ ነው፡፡ በወያኔም ጊዜ ይህን ፀረ ሕዝብ ቡድን ነፃ አውጪ ብለው በስሩ የተኮለኮሉት ጥቂቶች አንዳልነበሩ ሁሉም ዜጋ ያውቃል፡፡ ቀስ በቀስ እስኪመታቸው ድረስ አብረውት በፈረደበት ሕዝብ ላይ ሊፈነጩ የተዘጋጁና የጀመሩም ቢሆኑ  ጥቂቶች አልነበሩም፡፡ በየሥርዓቱ ሕዝብን ከድተው ለጨቋኙ  ያደሩ የመኖራቸውን ያክል አረመኔዎችን በቆራጥነት ተፋልመው ህይወታቸውን ለሀገርና ለሕዝብ የሚሰጡም በርካታ ናቸው፡፡ እነዚህም የጠላትን እውነተኛ ገፅታ የሚያውቁና የተጨባጭ ሁኔታውንም ሳያደናግሩ የሚረዱ ሆነው በመገኘታቸው በየወቅቱ ጠላትን በሚገባ ተፋልመዋል፡፡ ዛሬም የወያኔ አገዛዝ በሰላምና ራሱ ምርጫ ብሎ በሚያሾፍበት ሂደት ሳይሆን የሚሸነፈው ባመረረና ሕዝብን ባስተባበረ ሁለገብ ትግል መሆኑ ቁልጭ ብሎ የሚታይ ነው፡፡ ይህን ሐቅ የሚሰርዝ ሆነ የሚክድ የትግል አማራጭ ሕዝብን ለቀጣይ ስቃይ የሚዳርግና ሀገርንም በወያኔ የሚያስጠፋ ነው፡፡**

**ኢሕአፓ በ**1964 **ዓ.ም. ቢመሠረትም ለመታወጅ የተወሰነ  ጊዜ ወስዷል፡፡ በህቡዕ መደራጀትና ለድርጅታዊ ትግል ሰፊውን ሕዝብ መቅረብና መሰብሰብ አዲስ ተልዕኮ ነበር፡፡ ይህን ተልዕኮ ድርጅቱ ተወጥቶ በወሳኙ ጊዜ ህልውናውን ለሕዝብ አሳውቆ ይፋ ትግሉን አካሂዷል፡፡ ኢሕአፓ ያነሳቸው መፈክሮች የሕዝብ ነበሩ፤ ዛሬም ናቸው፡፡ ከየካቲት** 66 **በፊትና ከዚያም በኋላ ኢሕአፓየሕዝብና የሀገርን ጥቅም አስቀድሞ ታግሏል፡፡ ወያኔ ለሥልጣን ሲበቃም ኢሕአፓ በ**1967 **ዓ.ም የጀመረውን ፀረ ወያኔ ትግል አፋፍሞ ለመቀጠል ተነሳ እንጂ  ለዘረኛው ቡድን ጊዜ እንስጠው፣ እንተባበረው፣ በምርጫ እናጅበው ወዘተ... ብሎ ታሪኩንም አላባለሸ፣ የሕዝብንም ትግል አላደናቀፈ ፡፡ ወያኔ ሕዝብን ከፋፍሎና እርስ በርስ አናክሶ ሊገዛ ሲነሳም ይህንን ደባ አጋለጠ እንጂ በብሔረሰብ ደረጃ ሊከፋፈል ወይም ከሀገር ቅርጫ ድርሻውን ሊውስድ አልተሯሯጠም፡፡ ባዕዳንም ለወያኔ ገብሩ ሲሉ ኢሕአፓ**

EthioLion.com

EthioLion



ጆሮ አልሰጣቸውም:: ስለዚህም በነሐሴ 26 የታወጀበትን ቀን ሲያከብር ወደኋላ መልከት ሲል ቃል ኪዳኑን አክብሮ በመታገሉ ና ዛሬም ቢሆን ትግሉን በመቀጠሉ ይኮራል እንጂ አያፍርም:: ዓመታትን በባዶ እየቀጠረ እሰየው የሚል ባይሆንም በትግል ፀንቶ ይህን ሁሉ ዓመት ማሳለፉና መቸም ቢሆን መቼ ለማንም ጨቋኝ ኃይል ሆነ ባዕድ አለመንበርከኩ ያኮራዋል-- የኩሩ  ሕዝብን ቅርስ አክብሯል፤ አስከብሯልና:: በትግሉ ሂደት ከውስጡ የበቀሉ ሙጃዎችንም በጊዜ ያረመውና ራሱን ያፀዳው ኢሕአፓ የታሪኩን ማህደር ሲከፍትና ሲያገላብጥ የክህደትን ጎራ ምንኛ እንዳጠቃና እንዳተራመሰ ሲያይ፤ ከሰፊው ሕዝብ ጋር በመሆን የተጓዘበትን መራራ ግና የህገራዊ ግዳጅ ጎዳና ሲያጤን ዛሬም የሕዝብ ዕንባ ባለመታበሱና ችግሮችም ባለመቀረፋቸው ትግሉም መቀጠሉ ተገቢ ሆኖ ያገኘዋል:: ትውልድ ብሔራዊ ግዳጁን ካልተወጣ ሀገር ከጥፋት አትድንም፤ ሉዓላዊነቷም አይከበርም:: የአሁኑ ትውልድ ግዳጅም ኢትዮጵያን ከወያኔ ጥፋትና ጥቃት ማዳን ነው::

የሕዝብ ጎራ እንዲጠናከር ሆነ የተጀመረው ትግል ከግቡ እንዲደርስ የሀገራችን መሠረታዊ ችግሮች መወገድ አለባቸው:: ዛሬ የኢትዮጵያ ችግርና ጠላት የወያኔ አገዛዝ ነው-- ለኢትዮጵያ ችግርዋነኛው ተጠያቂ የወያኔ አገዛዝ ነው:: ሀገርን በስቃይና በመከራ ያደባየው ችግር ይወገድ ዘንድ ወያኔን ማስወገድ ያስፈልጋል ማለት ነው:: ለዚህም ነው የትግሉ ዋና ዓላማ በወያኔ ቧልት ገብቶ ዳንኪራ መርገጥ ሳይሆን ወያኔን መፋለም ሆኖ የሚገኘው:: ኢሕአፓ ሲመሠረት ሆነ ሲታወጅ የሕዝብን ጠላቶች እንፋለም የሚል የትግል ጥሪውን እንዳሰማ ሁሉ ዛሬም ቢመርም ባይጥምም መልዕክቱ ያው ነው-- የወያኔን አገዛዝ በትግል እናውድም የሚል ነው:: ሌላ አማራጭ ተገኝቶ ቢሆን ኖሮ ከማንም በፊት ኢሕአፓ ከፍልሚያ በመለስ ያለውን መንገድ በተጓዘበት ነበር:: የሀገርን ጠላት ከመፋለም በመለስ ያለው አማራጭ ግን የመገበር፤ ባርነትና ውርደትን የመቀበል በመሆኑ የኢትዮጵያን ታሪክና ክብር የተቀበለው ኢሕአፓ የሚቀበለውና የሚከተለውም ጎዳና አይሆንም:: በፀረ ወያኔ ትግል ኢሕአፓ ከፍተኛ መስዋዕትነትን ከፍሏል--ከሰሜን እስከ ደቡብ፥ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ ድረስ፤ ከአሲምባ እስክ ጎንደር ጎጃም፤ አልፎም አዲስ አበባ እስከ አርባ ምንጭ አያሌ አባላቱን በዚሁ ትግል አጥቷል:: ይህ መከራና ሰቆቃ ደረሰብኝ በሚል ግን ኢሕአፓ ትግሉን ሊያቆም ወይም አንዳንዶችም ሊመክሩ እንደ ሞከሩት ከወያኔ ሊሞዳሞድ መቸም መጠበቅ የለበትም:: የጀመሩትን መጨረስ ሕዝባዊ ግዴታ ነው:: እምቢኝ ለከሀዲና ባንዳ ቡድን/አገዛዝ ማለት ደግሞ ኢትዮጵያዊነት ነው:: የኢሕአፓ በደም የተፃፈታሪክ ደግሞ የኢሕአፓን ፅኑ ኢትዮጵያዊነት  ያረጋግጣል::

ዓመት አልፎ ዓመት ሲተካ ለመጪው ትወልድ አይለጉት ሀኬት፤ አያስተላልፉት ግዳጅ በጫንቃችን ላይ እየወደቀ፤  ውድ ሀገራችን ስትጮህ የዝሆን ጆሮ ይስጠን ማለቱ ሐጢያት

EthioLion



**-ሀራም- ሆኖእየታየን ብንደማም ብንሰቃይም የትግልን ሰንደቅ ማውለብለብ ግዴታችን ነው ብለን ተቀብለናል፡፡ ትግሉ ሲመርና አላባራ ሲልም ጣመን ባንልም በቃን አንገሸገሸን፤ ተውነው አበቃን ማለቱ ለኢሕአፓ የሚዋጥለት አልሆነም፡፡ የሚያለቅሱ ዜጎች፥ የሚበደሉ ወገኖች፥ ክብሯ የተደፈረ ሀገር እስካለች ድረስ የኢሕአፓ ትግል ሲቀጥል ቆይቷል፤ ወደፊትም ይቀጥላል፡፡**

**የኢትዮጵያ ሕዝብ በጠላቶቹ ላይ ድልን ይቀዳጃል!**
**እናቸንፋለን!!**

EthioLion.com